# ዴሞክራሲያ

* የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ልሳን *

ዴሞ ቅጽ 33 ቁ. 10 ሐምሌ 2000 ዓ.ም .


## ትግል ሲሉ፤ ትግል ስንል

ዴሞክራሲ፥ ኢትዮጵያዊነት፥ መብት፥ ትግል--ቃላት ክቡር፤ ቃላት ውጥንቅጥ፤ ቃላት ባለ ብዙ ትርጉም። የፖለቲካው መድረክ በሀቀኞቹ ታጋዮች ብቻ ሳይሆን በተለይም በአስመሳዮች ተጨናንቆ፤ የሁሉም ቀረርቶ በግልቡ በቃል ደረጃ ተመሳሳይ መስሎ ሲያደናግር በየጊዜው ትግል ሲሉ ስንል በሚል ማብራራት የግድ ሆኗል።

ለሀገር ለወገን መታገል ለመጪው ትውልድ አይለጉት ሀኬት ነውና የጭቆና ሰደድ እሳት ለብልቦ ሳይፈጀንና ሳይጨርሰን ለማስቆም፤ ጎበዝ ተነስ፤ ጀግኒት ተነሽ ብለን፤ ቁጣን በተወለወለው ሽጉጥ፤ክላሺንና መትረየስ አጅበን፤ ፍቅሬ ሆይን በጃሎ ተክተን፤ በዚያ ቀውጢ ጊዜ፤ የሽቶን ቦታ ባሩድ ተክቶ ሲሰነፍጠን ነጋ ጠባ ፈሪ ተለይ፤ አስመሳይ ዞር በል ማለቱ የግድ እንዳይሆን ከወዲሁ የትግላችንን ይዘትና ዒላማ ለይተን የፀዳ ጎራን ይዘን ልንነሳ ይገባናል። ትግል ስንል ማለቱ መቅደሙ ለዚህ ነው። ዴሞክራሲን ከአፉ የማይለይ የአምባገነንነት እጮኛ መበርከቱን በምድር ላይ የሰርቶ አደሩን ገነት ሊያመጣ ቃል ከገባው የቀይ ሽብር አውሬ ኮለኔል፤ በቀን ሶስቴ አብልቶ ሊያጠግበንና በዴሞክራሲም ሊያጥነን ምሎ ከነበረው ጠባብ ነፍሰ ገዳይ ተምረናል። ፍራንክ ላቃጨለ ባዕድ ነፍሱን የሚሸጠው ሁሉ፤ ከኢትዮጵያዊነት በፊት ብሄረሰቤ ይገልጠኛል ባዩ ሳይቀር በኢትዮጵያዊነት ሊነግድ መራወጡንም ነጋ ጠባ ሳንወድ መታዘብ ተገደን ቆይተናል። መብት ለጭቁኑ መፈክርን ከአፋችን ነጥቀው ዴሞክራሲ በገደብን ለፍፈው የዴሞክራሲን ደብዛ በሽብርና በጠራራ ፀሀይ ግድያ ያጠፉትንም አገዛዞች ተሸክመን ከርመናል። ከሕዝብ ጎራ ነን ባሉበት አፋቸው ታጋዮችን አውግዘው ከገዢዎች ደም ረጋጭ ጫማ ስር የተደፉትንም እንደዚሁ ታዝበናል። ሲሉ ስንል ብሎ የሚለየን መስመርና አቀዋም፥ እምነትና ቃል ኪዳን ጥርት ባለ መንገድ --በተለይም የሚያደፈርሱ ሲፈሉ--ማስቀመጡ አስፈላጊ ነው።

በአሁኑ ወቅት ትግል በማን ላይ፤ ትግል ከማን ጋር፤ ትግል ለምን የሚሉት ጥያቄዎች ሁሉ በአዲስ ምላሽን ጠያቂ ሆነው የቃላት ጨበጣው በተወሰኑት ዘንድ ተፋፍሞ ይገኛል። ትግል እናካሂዳለን ግን ጠላት የለንም ከሚሉት ጀምሮ ትጥቅ ትግል የሚሉትን ገዝ ለሁ ከሚሉ ቤተክህነት የማታውቃቸው አስመሳይ የፖለቲካ ቁሶችን ጨምሮ ትግል ምንድነው የሚለውን ተገቢ መልስ እንዳንሰጥ እያደናቀፉን መሆኑ እየታየ ነው።

ትግል ስንል የወያኔን አገዛዝ በሕዝብ ጠላትነት ፈርጆ አገዛዙን ለማስወገድ የሚካሄደውን ነው:: ትግል ሲሉ የግል ጥቅማቸውን አስቀድመው ከመሞት መሰንበትን እያነበነቡ ለባለነፍጥ ገዢዎች መንበርከክን ነው:: በሁለቱ አቅዋሞችና አመለካከቶች መሀል ያለው ልዩነት በነፃነትና ባርነት መሀል ያለውን ዓይነት ነው:: አንደኛው የትግል መንገድ በእርግጥም ውጣ ውረድ ያለበት፤ መስዋዕትነትን ጠያቂ፤ መከራና ስቃይንም አሳቃፊ ነው:: ዛሬ በትግል ስም የሚካሄደውን የመድረክ ግብግብ ሳይሆን፤ በትጥቅ ትግል ስም የሚካሄደውን የወረቀት ውጊያ ሳይሆን ትግል ስንል መረር ኮስተር ያለውን፤ ሰውን የሚያስለካውን፤ ወኔ ፅናትን የሚፈትነውን ነው:: ከገዢ ጋር መለሳለሱን ፈላጊው አማራጭ ደግሞ ሕዝብና ሀገርን የሚያዋርደውንና ደም የሚያስተፋውን አገዛዝ እንኳን ጠላት ብሎ ለመፈረጅ የሚተናነቀውና ሰለጠነ ሲሉ አበደ በሉ እንደተባለው በመሰልጠን ሽፋን እጅ ሰጥቶ ተዋርዶ እንደ ባርያ መገዛትን የሚያቀነቅን ነው:: በሁለቱ ተፃራሪ አቅዋሞች መሀል ብዙውን ጊዜ አፍዝ አደንግዝ አደናጋሪ ቃላት ስለሚወረወሩ ልዩነቱ እየተድበሰበሰ አስመሳዩም ሀቀኛውም ሁሉም ተቃዋሚ እየተባለ፤ የከዳው ሳይወገዝ፤ የፀናው ሳይወደስ፤ ሀቁ ነጥሮ ሳይወጣና ጎራ ሳይፀዳ መጓዝ የግድ ሆኖ የሕዝብ ትግል ተጎድቷል::

ትግል ስንል ነጋ ጠባ ሕዝብ ያወቀውንና የሰለቸውን ዜና ማብሰሩ ሊሆን አይችልም:: የወያኔ አገዛዝ ፀረ ሕዝብነት ቢያንስ ለብዙሀኑ ምስጢር አይደለም:: ስለዚህም ትግል ስንል ይህን ጠላት ለማስወገድ ምን መደረግ አለበት የሚለውን ምላሽ ሰጪ ሊሆን ይገባዋል:: ትግል ወሳኝ የተፃራሪ ኃይሎች ፍልሚያ ነውና በባዕድ ሀገር ለሆነ ሥልጣን ተወዳድረው ሲሸናነፉ እንደሚጨባበጡበት ሂደት ሊሆን አለመቻሉን ማወቅ መቅደም አለበት:: በኢትዮጵያ÷ ገዢዎች በንፁህ ዜጋ ደም የሚታጠቡ ጨካኞች ናቸውና ሲጠጓቸው ይከረፋሉ - የግል ጥቅምና የሆድ ፖለቲካ አፍንጫውን የዘጋበት ሰው ካልተሆነ በስተቀር:: ቅራኔው የጎመራ ሆኖ ደምን ያፋሰሰ ነውናም በድል አድራጊ ተሸናፊ እንጂ በመጨባባጥ የሚፈታ ሊሆን አይችልም:: ይህ ያልሆነው ሕዝብ ወግዱ የምን ዕርቅ ብሎ “ ስላከረረ ” ሳይሆን ገዢዎች ይባስ ብለው የምን ዕርቅ የምን መግባባት ብለው በሕዝብ ላይ ስለታበዩ ነው:: ግንቦት 97ን ያጤኗል:: በዚህ ሁኔታ የለወጥ አዋላጁ ዕርቅና መቻቻል ወይም ጠላትን ወዳጅ ብሎ መለመን ሳይሆን ጠላትን የሚያስወግደውን መራራ ትግል ማካሄድ ብቻ ይሆናል:: ለዚህም ነው በሰላም ትግል ሽፋን ለአገዛዙ እጅ መስጠትን የሚሰብኩ ዘመናዊ ፈሪሳውያን ወይም ጠምጣሚዎች (ወይም ምሁሮች) የሕዝብን ትግል ጎጂዎች ሆነው የሚገኙት:: ከግንቦት 97ኡ ምርጫ ከተከተለው ፍጅት በኋላ ግንቦትን የወለደው ሁኔታ ሁሉ ቅንጣትም ሳይቀየር በዚያው በገደላ ገደሉ መንገድ በ2002 እንጓዝ ብሎ መስበኩም በዝምታ ሊታለፍ የሚችል አይሆንም::

ትግል ስንል ዛሬ ልናስወግደው የምንፈልገው ላይ ብቻ ማተኮርን ጠያቂ ሳይሆን መጪውንም በዕይታ ማስገባትን የግድ የሚል ነው:: አፄው ይውደቁ እንጂ ግድ የለም ማለቱ የመኮንኖችን ሽብርተኛ ቡድን በላያችን አምጥቶ ትውልድ ተመትሯል፤ አልቋል:: ደርግ ይወገድ እንጂ የባሰ አይመጣም በተራው ፀረ ኢትዮጵያ የሆነውን ከሀዲ የወያኔ ቡድን አስፍሮብናል:: ዛሬም ከመለስ ዜናዊ ጠባብ ብሄረተኛ ቡድን የከፋ የሀገርና የሕዝብ ጠላት ሊመጣ የሚችል መስሎ ባይታየ ም የማይመጣበትን ሁኔታ

ለማረጋገጥ ከወዲሁ ማሰብ እንዳለብን ግልፅ ነው። አገዛዙ ጉልቻ ቀይሮ የጎረና ወጡን አሁንም በቀን ሶስቴ ባይችል እንኳን ቢያንስ በሁለት ቀን አንዴ ብሉልኝ ሊል ሴራ እየሸረበ ነው። ከዚያ ባሻገር የለውጥ መልኳ ሥር ነቀል መሆኗ መሆኑ መረሳት የሌለበት ነውና ዛሬ ከትላንት ይሻላል በሚል ዛሬም ሬሳ እየቆጠርን በደል እየቻልን መጓዝ የለብንም። የሕዝብ መብት ከቶም የማይገደብበት፣ ንፁህ ዜጋ የማይገደልበት፣ የህግ የበላይነት የሚከበርበት፣ የሀገርንና የሕዝብን ቁስል የሚያክምና የሚያድን ሥርዓት ያስፈልጋል። ያለፈውን ተኪዎች ይብሶች ከሆኑ ግን ዳግም ለፍቶ ደምቶ መና መሆን ይመጣልና ይህንን ሰቆቃ ለመድገም ተባባሪ ልንሆን አይገባንም። ስለዚህም ወያኔና ሥርዓቱ ሲወገዱ በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እንጂ በሌላ ጨቋኝ ሥርዓት - ያው ሆነ ለዘበ - እንዲተካ ሕዝብ መፍቀድ የለበትም። ለዚህም ነው ሕዝብ መደራጀትና ነቅቶ መገኘት ያለበት - ካለፈው ለመማርና የትላንትን ስህተት ነገ ላለመድገም።

ለተቀማጭ ሰማይ ቅርቡ እንደሚባለው ሳይዋጉ የሚማርኩና የሚያስገብሩ የአፍ ጦረኞች በዝተዋልና ትግሉ የሚጠይቀው መስዋዕትነት ሲከፈል ድርጅትን በ “አስጨረሠ” ክስ የሚያዋክቡና የነገን ትግል የሚያደናቅፉ መብዛታቸው አልቀረም። ትግል ሲሉ መትረየስን በምላስ መተካት የመሰላቸው እንዳሉ ትላንትም ዛሬም አይተናል። ትግል ግን ይቺ ሀገር የእኔ ናት፣ መብቴንም ማንም አይገድብም ብሎ የተነሳ ሕዝብ በጠላቱ ላይ የሚያካሂደው እስከሆነ ድረስ የፍልሚያውን አውድማ የሚያውቁት እንዳሉት ሁሉ የሥር ነቀል ለውጥ ትግል የእራት ግብዣ ወይ አስረሽ ምቺው አይደለምና ደም መፍሰሱን፣ መስዋዕትነት መክፈሉን ማምለጥ አይቻልም። የአብዬን ለእምዬ እስካልሆነ ድረስ አስጨራሾቹ የሚታገሉት ድርጅቶች ሳይሆኑ ጨራሾቹ ገዢዎች ወይም አገዛዞች ናቸው። ይህን በሚገባ ከተረዳን ትግል ስንል ለሚከፈለውም ዋጋ ዝግጁ መሆናችንን ጠያቂ መሆኑን ማወቃችንንም ይጠቀልላል። ትግልን በነጋዴ የትርፍ ኪሳራ ስሌት ለማየት መነሳቱ ብዙ ባያስኬድም የሚከፈል ዋጋ መኖሩ ግን የማይታለፍ ወይም የማይታበል ነው። በትግሉ ሂደት አላስፈላጊ ጉዳት የሚያስከትለውን መቀነስ ወይም ማስወገድ ሲገባ ሁሌም ይህ የማይሳካ ነውና ጉዳት አልባን ትግል ፈልጎ ትግል አልባ ከመሆን መደረግ ያለበትን ትግል ታግሎ መስዋዕትነትንም መቀበል ተገቢ ነው። ትግል ስንል የማን ቤት ጠፍቶ የማን ሊለማ ፉከራችን ሥረዓተ-አልበኛ ሳይሆን የሰከነ ድምዳሜንና እርምጃን አንፀባራቂ መሆኑ መታወቅ አለበት።

ትግል ስንል ሕዝብና ገዢ ቡድንን የሚያምታታ ባይሆንም ይህ ከፋፋይ ቡድን የራሴ ሕዝብና ክልል የሚለውን በማስቀደምና በመጥቀም የፈጠረው ውጥንቅጥ ደግሞ በቾልታ የሚታለፍ አይደለም። የትግራይ ምሁራን ብቻ ሳይሆኑ ተቃዋሚ ነን ብለው ከመለስ ዜናዊ የተለዩት የወያኔ ቁንጮ መሪዎችም ቢሆኑ ያለውን አገዛዝ የራሳቸው (የትግራይ) አድርገው በመውሰድ ዛሬም የጠባብ የበላይነታቸውን ለማስጠበቅ እንደሚንተከተኩ መታዘብ የተገደድነው ጉዳይ ነው። ስንቱ የትግራይ ምሁር ኢትዮጵያ ብሎ እንዳልተሰዋ ሁሉ፣ ስንቶቹ የትግራይ ተወላጆች የኢሕአፓ አባላት ወያኔን ሲፋለሙ እንዳልተሰው ሁሉ የዘ ድሮዎቹ የትግራይ ምሁራን በአብላጫው ሥርዓቱ የእኛ ነው፣ አጥፊው መለስ ነው ዓይነት አቅዋም ይዘው “ሥርዓታቸውን” ለማደስና ለማስቀጠል እየተጣጣሩ መሆናቸው የሚካድ አይደለም። ገዢው መደብም

መገልበጪያዬ ትግራይ ነው በሚል ድልዳሉን ማመቻቸቱ የሚጠበቅና የሚታይ ነውናም ሕዝብን ከሕዝብ በሚያፈራቅቅ ፖለቲካው እየገፉ በመሆኑ የተበሳጨው ክፍል በጥቅሉ ወደ ማውገዝ ስህተት እንዲገባ ማጠየቂያ እያዘጋጀ ነው:: በአጭሩ፤ የወያኔ አገዛዝ የትግራይን ሕዝብ ከቀሪው የኢትዮጵያ ሕዝብ ለመነጠልና ለማጋጨት ሲጥር የትግራይ ምሁራን ይህን ለማክሸፍ በሚደረገው ትግል ሚናቸው ኢምንት ሆኗል:: ነገ የዚህ ሁኔታ አንደምታው በሕዝብ ዕልቂት መለስ ዜናዊ የሚመኘውና ይመጣል የሚለው ሩዋንዳ ተከስቶ የኢትዮጵያ ቀና ታሪክና የሕዝቧም አንድነት እንዳይበላሽ ሀቀኛ ሀገር ወዳዶች ከዛሬው መጨነቃቸውና መፍትሄ መፈለጋቸውም ግዳጅ ነው::

ትግል ስንልም ግቡንም ከግቡም የሚያግደውንም የሚያውቅ ነው:: ትግል ብለው ጠላትን ወዳጅ ብለው ፈርጀው የሚነሱ ከማንና ለምን እንደሚታገሉም ያልገባቸው ናቸውና ባለው የጭቆና ቀንበር ሥር ከመሽጋሸግና የራሳቸውን የግል ቀዳዳ ከመፈለግ አያልፉም:: ትግል ስንል ወዳጅ ጠላቱን በሚገባ የለየውን ነው:: በስሜተ ፈረስ ጋልቦ በቀቢፀ ተስፋ ተኮርኩሮ ግራ ቀኙን ሁሉ ጠላት ብሎ አንዲት ጦሩን በዓለም ላይ የሚሰብቀውን አይደለም:: ይህ የጠላትን ጎራ የሚያሰፋ አቅዋም ለለፋፊው ጊዜያዊ እርካታን ይሰጥ ይሆን እንጂ ተግባራዊም ሊሆን የማይችል መሆኑ የተረጋገጠ ነው:: መላ ሕዝብን በጠላትነት ፈርጀው ውሱን ዓላማችንን አገኘን የሚሉት ዛሬ በምን ሁኔታ ላይ እንዳሉ ዓይናችን ወደ ሰሜን ብቻ ማማተር የለበትም:: ኢትዮጵያ ሀገራችን በአፍሪካ ቀንድና በመላ አፍሪካ ከያዘችው ቦታና ክብደት የተነሳ፤ የአባይ ወሀ ዋነኛ ምንጭ በመሆኗ፤ የነፃነት አርአያ ሆና በመባጀቷ፤ ...ወዘተ በዚህም በዚያም የማይተኙላት ጠላቶች አሏት:: እነዚህም የራሳቸውን ብሔራዊ ጥቅም እንደሚጠበቀው ሲያሳድዱ የኢትዮጵያን ጥቅም መዳፈራቸው የነበረ፤ ያለና የሚቀጥልም በመሆኑ ትግል ስንል የሀገራችንን ብሔራዊ ጥቅም ለማስጠበቅና ሉዓላዊነቷንም ለማስከበር መሆን አለበት:: ኢትዮጵያ ላይ ያሸመቁትን ሁሉ ለመከላከል መቻል ያስፈልጋል::

ትግል ስንል የጥቂት ምርጥ ጀግኖች ትግል ማለታችን ሳይሆን ወይም ዘንድሮ ፈሊጥ ሆኖ እንደሚባለው የሰለጠኑ ምሁሮች ጉራማይሌ እሰጥ አገባ ሳይሆን ሰፊውን ሕዝብ ያሳተፈ ተጋድሎ ማለታችን ነው:: የሕዝብ ተሳትፎ የይስሙላና የአፋዊ ብቻ ሳይሆን በገቢር መረጋገጥ ያለበት መሆኑ ድል አለሰፊው ሕዝብ ተሳትፎ ሊሳካ አለመቻሉን በሚያውቁት ሁሉ የታመነበት ነው:: ሕዝብን የሚተካ ፓርቲ ወይም ድርጅት ወይም የምሁር ስብስብ ሊኖር አይችልም:: ሕዝብ ያልተሳተፈበት ትግልም ከንቱ ሆኖ መቅረቱ የሚታወቅ ነው:: በመሆኑም ትግል ስንል የድርጅቶችና የምርጦች የተለየ ተልዕኮ ሳይሆን ምልዓተ ሕዝቡን አቅፎ ሊያሳትፍ የሚችል መሆን አለበት ለማለት ነው:: የብዙሀኑ ተሳትፎ ማለትም ሁሌምና በግድ በድርጅቶች መሀል በሚፈጠር ግንባር ይከሰታል ማለትም ስህተት ነው:: የተባለው ህብረት ሊፈጠርና ሊጠናከር ከቻለ መልካም ሲሆን ዋናው ግን ሰፊውን ሕዝብ ሊያሰባስብ በሚችል መርሀ ግብርና መፈክሮች ዙሪያ መንቀሳቀስ መቻል ነው:: በየካቲት 66 ኢሕአፓ ብዙውን የህብረተሰብ ክፍል በዙሪያው ሰብስቦ ሊያታግልና ሊታገል ችሎ እንደነበር የታየ ነው:: የህብረተሰቡ ልዩ ልዩ ክፍሎች በየብሶታቸውና በጋራ ጥያቄያቸውም ዙሪያ

ሊሰባሰቡና ተቀናጅተውና ተባብረውም ሊታገሉ ይችላሉ:: የወያኔ ቡድን ሥልጣን ከያዘ ወዲህ ብዙሀኑን የሚያስተሳስሩ ብሶቶች--ለምስሌ የኑሮ ውድነት፤ የሀገር መሬት ለባዕድ መሰጠቱ፤ የሰብዓዊ መብት መረገጡ--አሉ:: ከዚህም በላይ የሀገርን ህልውና ማስጠበቁ ቀዳሚና ዋና ሆኖ ይገኛል:: ሀገራችንን ከጥፋት እናድን፤ መብታችንን እናስከብር በሚል አብዛኛው ኢትዮጵያዊ በጋራ ሊታገል ይችላል:: ይህን የጋራ ትግል መንፈስ በድርጅትና በተጨባጭ ትግል አጅቦ ማራመድ መቻል አለመቻል ለድል ዋና ጥያቄ ይሆናል:: ስለዚህም ትግል ስንል ብዙውን ሕዝብ በትግሉ ለማሰለፍ መቀስቀስ ማደራጀትንም የሚመለከት ይሆናል::

ብርሌ ከነቃ እንደሚባለው አገዛዞቸና ሥርዓቶች ሊጠገኑ ሊሞራረዱና ሊሻሻሉ ያቅታቸዋልና ያለው መፍትሄ መወገዳቸው መሆኑ ማከራከር ባይኖርበትም አሁንም በዚህ ላይ ውዥንብር በመኖሩ ትግል ስንል ከገዢዎቹ ጋር ተግባብቶ ያለውን ሥርዓት ቀሰ በቀስ ለመለወጥ መዋደቅ ነው የሚሉ አሉ:: ትግል ስንል በእኛ በኩል የጥገና ለውጥና ወያኔ ሊገናኙ የማይችሉ ናቸው በሚል ያለፉትን 17 ዓመታትም በዋቢ ጠቅሰን መፍትሄው ሥር ነቀል ለውጥ ነው እንላለን:: የሚነቀለውም የወያኔ አገዛዝ ሥርዓት መሆኑን ጫና ሰጥተን እናቀርባለን:: የአፄ ኃይለሥላሴን አገዛዝ ለመታገል ስንነሳ ቸኮላችሁ፤ ጠመንጃ ናካሽ ሆናችሁ...ወዘተ ብለው ያወገዙንና ኋላም ለእነእንዳልካቸው መኮንን ጊዜ እንስጣቸው ያሉት ያው በመጨረሻው አባዜያቸው ነድት ነድቶ የፋሺስቱ ደርግ አማካሪና አጃቢ አድርጎ ለጥፋት እንደዳረጋቸው አይተናል:: በሕዝብ ላይ አመኔታ የጎደላቸው ሁሉ፤ ሁሌም የትግሉን ሂደት ሊያቆሙ የሚነሱትና በጥገና ለውጥ እንገደብ፤ አደብ እንግዛ፤ እየተገዛን እንታገል፤ ተንበርክከን እናምፅ ብለው የሚሰብኩት በትግሉም በሕዝብም ላይ እምነት ስለሚጎድላቸው ነው:: ትግል ሲሉ ከጠዋቱ ተስፋ መቁረጥን አዝለው ነው:: መፅሐፉ እንዳለው ግን እምነት ተስፋ ስለምናደርገው ነገር የሚያስረግጥና የማናየውንም ነገር የሚያስረዳ ነው:: ጭቆናውና በደሉ እንደዛሬው በዝቶና ተበራክቶ ባለበት፤ የሕዝብ ጠላት በኃይሉ ተመክቶ በሚያቅራራበት፤ ተቃዋሚ ድርጅቶች የተባሉት መፍረክረክ ሲታይባቸው፤ ጠላት በባዕዳን ተደግፎ ሲኩራራ፤ ችግር በዝቶ ወገን ሰብዕናው ሲፈተን ማለትም ጨለማው ጥቅጥቅ ያለ ሲመስል የነገ ብሩህ ቀን ተስፋ ይኖር ዘንድ ጠንካራ እምነት በኢትዮጵያ ሕዝብ አቸናፊነት ላይ ሊኖረን ይገባል:: ይህ እምነት ካለ ዛሬ የማናየውን ድል መጪ መሆኑን መረዳት አንችላላን:: ትግል ስንል በሕዝብ አቸናፊነት ላይ ሙሉ እምነት ያለውና ፀረ ሕዝቡን ሥርዓት ሊያድሰ ሳይሆን ሊያፈርስ የተነሳውን ማለታቸን ነው::

ወጣም ወረደም ግን ትግል ትግል ነው:: ስለ ትግል ማውራት መፃፍ ማለት አይደለም:: ትግላችን እንደችግራችን ዘርፈ ብዙ መሆኑ ባይካድም ትግል ስንል በተጨባጭ የሚካሄድ ትግልን ማለታችን ነው:: የድርጅቶችን ህልውና ወይም ሚዛናዊና ጠቀሜታ መለኪያውም ይህ ትግል ብቻ ነው:: ዛሬ እንደ አሸን የፈሉ ቡድኖች እውን የሚታገሉ ድርጅቶች ናቸውን ብሎ ጠይቆ ምላሽ ለማግኘት እውን ተጨባጭ ትግልን እያካሄዱ ነወይ፤ አገዛዙን እየጎዱና እያሰጨነቁ ናቸው ወይ የሚለውን መመርመር ያስፈልጋል:: ተግባር ዋና ነው:: ቃላት ክቡር ናቸው ግን መፈተኛው ተግባር ነው:: የወያኔ አገዛዝ መሪ ተቃዋሚ ይቃወም ግን መደራጀት አይሞክር ብሎ ሲያሾፍ ያንፀባረቀውን ዕብሪት ወደ ጎን ብንተው እንኳን ድርጅትና

ተከታዩ ተጨባጭ ትግል ዋና መሆኑን ማመኑን፥ መስጋቱን የሚያሳይ ነው፡፡ ለዚህም ነው አንዳንዶች ሰላማዊ ትግል ወይስ የትጥቅ ትግል በሚል አላስፈላጊ ግንብ ገንብተው በመነታረክ ሲባሉ ዋናው ጥያቄ በዚህም በዚያም ማውራቱ ሳይሆን መታገሉ ነው ስንል ደግመን ደጋግመን ያሳሰብነው፡፡ የሕዝብን የሙት ከተማ አድማ ሥራ ላይ ማዋል ሳይሆን እያከሸፉ፣ በረሀ ሳይወጡ በወረቀትና ሀሰት መግለጫ አማካይነት የወያኔ ወታደርን እየገደሉ ታገልን ወይም ታጋይ ነን ማለት አይቻልም፡፡ ነፋስ ስንዴን ማፍራት አይችልምና በዚሁ መሰረት ወሬና ስለትግል አውርቶ ከትግል መራቅን አስወግዶ ወደ ትግል ሜዳ ወደ ተግባር መሰማራትን ማስቀደም ያስፈልጋል፡፡ ትግል ስንል ይህን ማለታችን ነው፡፡ ሊረሸኑ ሲሉ፣ ስየል ሲቀበሉና ሲሰቃዩ ሁሉ በጠላት ላይ እየተፉና ትግሉ ነው ሕይወቴ፣ እናቸንፋለን እያሉ በጀግንነት የሞት ፅዋን የጠጡ ብዙ ሺ አባላት ያፈራው ኢሕአፓ ትግል ሲል የዚህን ትርጉም ጠንቅቆ እንደሚያውቅ መዘንጋትም የለበትም፡፡

ከተለወጠ ጊዜና ሁኔታ ጋር አስፈላጊውን የመርህ ግብርና የትግል አካሄድ ለውጥ ማድረግ ተገቢ ቢሆንም በለውጥና መስልጠን ሽፋን አወቅን ብሎ መፅሀፍ ማጠብ መቆም ያለበት ነው፡፡ ትግል በይዘቱ ከዘመን ዘመን በተለያየ መልክ ቢንፀባረቅም ትላንትም ዛሬም ግን ዋናው ይዘቱ አንድ ነው--የሕዝብን ጠላት መታገል፣ ሥር ነቀል ለውጥን ማረጋገጥ፣ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን መመሥረትና የሀገር አንድነትን ማስከበር፡፡ ከዚህ ውጪ የሚታየን ሆነ የሚገባን ትግል የለም፡፡ ትግል ስንል ተነሱ እንታገል ብሎ በትግል ለመሰማራት እንጂ ስለ ትግል እናውራና በዚያው እናብቃ ማለታችን አልነበረም፣ አይደለም፣ መቸም አይሆንምም፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝብ በትግል የወያኔን አገዛዝ ያስወግዳል!!
በትግላችን ሀገራችንን እናስከብር!!
እናቸንፋለን!!